# የፓርላማውን ውሎ የማያንፀባርቁ መሠረተ-ቢስ ትችቶች

**በኃይሉ አስረስ 05/04/13**

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት በአንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 11 ላይ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ፣ በመንግስት ስለ ተከናወኑ ተግባራትና ስለ ወደፊት ዕቅዶች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ከመሰንበቻው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው የመንግስታቸውን የስምንት ወራት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረባቸው ይታወሳል። በሪፖርታቸው ላይም ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱት ጥያቄዎች ተገቢውን ማብራሪያና ምላሽ መስጠታቸውም አይዘነጋም።

ይሁንና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው ያቀረቡትን ሪፖርትና ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ ተከትሎ፤ ወትሮም ቢሆን የራሳቸው አጀንዳ ሳይኖራቸው በሌላው አጀንዳ ላይ እየተንጠላጠሉ ተራ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚራራጡ አንዳንድ የተቃውሞው ጎራ ወገኖችና የሚዲያ ውጤቶች መሠረተ-ቢስ ትችቶችን ሰንዝረዋል፤ እየሰነዘሩም ነው። በተለይም የሀገራችንን ህዝቦች የተመፅዋችነት ገፅታን በመቀየር ላይ ስለሚገኘው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ የሀገራችንን ስም ማጉደፍ ስለማይሰለቸው ስለ ሂዩማን ራይትስ ዎች የርዕዮተ-ዓለማዊ ክስ፣ ስለ ቱሎው ኦይል ኩባንያ ነዳጅ ፍለጋ እና ሶማሊያ ስለሚገኘው ሰራዊታችን ቆይታ አቶ ኃይለማርያም ያላሉትን ጭምር ራሳቸው በማከል ብሎም ተባራሪ ወሬን አንጠልጥለው 'እንዲህ ያሉት ጉዳይ ትክክል አይደለም' እያሉ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖርላማው ውሎ ውጪ የራሳቸውን የአሉባልታ ፓርላማ ፈጥረው ሲያላዝኑ ሰንብተዋል። እናም የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እነዚህን የተሳሳቱና "ራስ ወለድ" ትችቶችን በመጠኑም ቢሆን በመዳሰስ ለማረቅ እሞክራለሁ።

አቶ ኃይለማርያም የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን አስመልክተው ከነኳቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ የኢንዱስትሪ፣ የኤክስፖርት ዕቅድ እንዲሁም ስራ አጥነትን ለማቃለል በዕቅድ ዓመቱ የተያዙት ትልሞች በበጀት ዓመቱን በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ እየተተገበሩ መሆናቸውን ነው። ሆኖም አዲስ አድማስ ጋዜጣ "በነፃ አስተያየት" አምዱ ስር (ምናልባትም የጋዜጣው ታዋቂ ሚርተኛ አቶ ዩሐንስ ሰ. እንደፃፉት ከብዕር አጣጣላቸው በመነሳት የምገምተው)፤ 'ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዕቅዶቹ አለመሳካታቸውን እያመኑ በተደጋጋሚ በተያዘላቸው ጊዜ ተፈፃሚ እየሆኑ ነው ማለታቸው አግባብነት የለውም ካለ በኋላ፤ ያለ አንዳች ሃፍረት ኢህአዴግ በ2002 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 'በስሜት' ተነሳስቶ ያዘጋጀው ዕቅድ አልተሳካም ሲልም በድፍረት

ይደመድማል።...እንግዲህ ልብ በሉ! የነፃ አስተያየት አምድ ፀሐፊው ከሙያቸው ውጪ ጥንቆላን እየተለማመዱ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዕቅዶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ እየተከናወኑ ናቸው እያሉ፣ ፀሐፊው ደግሞ አውቀው ላለማመን እንጂ እንደማይሳኩ እርሳቸውም ያውቃሉ እያሉን ነው። ይህ ደግሞ እርሳቸው ካሉት ጋር ፈፅሞ የማይገናኝ ከመሆኑም በላይ፣ ፀሐፊው በጨለማ ውስጥ የሚያሚርተቱትን ህልም የግድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሉላቸው መፈለግ ነው። እናም ዕውነታው ጨለምተኛውና ሰቆቃዊው ፀሐፊ እንዳሉት ሳይሆን፣ አቶ ኃይለማርያም ለፓርላማው እንዳስረዱት የኢንዱስትሪውና የኤክስፖርቱ እመርታ ከፍ በማድረግ እንዲሁም የስራ አጥ ቁጥርን በመቀነስ ረገድ ተግባራቱ ባለፉት ሁለት የልማት ዓመታት በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ተከናውነው አጥጋቢ ውጤት አምጥተዋል።

የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በተመለከተ ጥቂት ጉዳዮችን ማውሳት ይቻላል። እንደሚታወቀው በገጠር የአርሶ አደሩን የካፒታል አቅም በማሳደግ የማኑፋክቸሪንግ ጥሬ ዕቃዎችን በብዛትና በጥራት በማምረት ቀስ በቀስ ወደ ኢንዱስትሪው መሸጋገር እንዲችል ዕቅድ ተነድፏል። በዚህም የገጠር ወጣቶችን የዕድሉ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሁም ሴቶች በቤት ውስጥ የሚሰሩትን ቀላል ስራዎችን በሂደት በፋብሪካ በመተካት ሙሉ በሙሉ ከቤት ውስጥ የኑሮ ጫና ለማላቀቅ ያለመ አቅጣጫ ተይዟል፡፡ በከተማው ደግሞ በአነስተኛና ጥቃቅን ስራ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ስራ አጥነትን በመቅረፍ በሂደት የሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚያድጉበት ሁኔታ መመቻቸቱ ይታወሳል–ዕቅዱ ሲደፍ። እናም በእስካሁኑ ጉዞ መንግስት በነደፈው አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን የማስፋፋትና የመደገፍ ስትራቴጂ መሠረት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጐችን ወደ ባለሃብትነት ወይም ወደ መካከለኛ ኢንዱስሪ መሸጋገራቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

እናም ባለፈው ዓመት 250 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሃብትነት /መካከለኛ ኢንዱስትሪ/ ሊሸጋገሩ ችለዋል፡፡ ታዲያ ይህ ተግባር የሚያመለክተው የአዲስ አድማሱ ጨለምተኛ ፀሐፊ "አልተሳካም" እንደሚሉት ሳይሆን፣ መንግስት ዘርፉን ለማሳደግ የቀረፀው ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤታማ መሆኑን ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ከተሸጋገሩት ውስጥም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጐች በኮንስትራክሽን ዘርፍ በማሰማራት ላይ እንደሚገኙ እኚሁ ግለሰብ ሊያውቁት ይገባል፡፡ ለአብነት ያህል የአዲስ አበባ ከተማን እንኳን ብንመለከት በ27 ማህበራት የተደራጁ ስድስት የስራ ተቋራጮች ሰርተፍኬትና እውቅና ተሰጥቷቸው ወደ ስራ ገብተው ውጤታማ መሆናቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ዕውነታም በአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት ዘርፍ የተገኘው ውጤት በሌሎች ግዙፍ ኢንዱስትሪዎችም እየተደገመ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ2004 ዓ.ም ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ምርቶችና የፋርማቲካልና የኬሚካል ውጤቶች የተገኘው ድምር ዕድገት ካለፉት ጊዜያት ጋር ሲነፃፀር ከ22 በመቶ በላይ እድገት ማሳየቱን ቢያንስ ሃቁን ጠይቆ በመረዳት ማወቅ ይቻላል። ይህም ዕቅዱ በትክክለኛ መስመር ላይ እየተጓዘ መሆኑን አብይ ማሳያ ነው፡፡ ዘርፉ እንደተቀናት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ሁሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ የሚፈለገውን የሰው ሃይል በአስተማማኝ ለማልማት ከቴክኒክና ሙያ እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የማቀራኘት ስራ በመደበኛ፣ በረጅምና በአጫጭር ስልጠናዎች የዘርፉ አቅም የመገንባት ስራ ተከናውኖ ውጤት ተገኝቶባቸዋል፡፡

በመሆኑም እስከ አሁን ለታየው ዕድገት በምክንያትነት የሚጠቀሱትን ለባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲሁም የተቀላጠፈ የፋይናንስ፣ የጉምሩክና የሎጅስትቲክ አገልግሎት ድጋፍ መስጠትና አስፈላጊ መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ ማምረት ቀጣይ ትኩረት የተሰጣቸው የሁለት ዓመት ስኬቶች ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በአግሮፕሮሰሲንግ፣ በኬምካልና ፋርማሲዩቲካል ዘርፍ የተገኘው ውጤት በ2005 ዓ.ም ይገኛል ተብሎ ከሚገመተው የ112 ነጥብ ሦስት በመቶ ብልጫ እድገት ለማስመዝገብ ግብ ተጥሏል፡፡ ለአብነት ያህል በ2004 ዓ.ም ከቆዳው ውጤቶች ብቻ 100 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ከተቀመጠው ዕቅድ አንጻር የተሻለ አፈጻጸም እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ባለፉት ሁለት ዓመታት በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍም ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከውጭ ሀገራት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይገቡ የነበሩ መለዋወጫና ማሽነሪዎች በሀገር ውስጥ መመረት ጀምረዋል፡፡ በተለይም የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ለኢንዱስትሪው ሽግግር ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኝ ማወቁ ከአንድ ፀሐፊ የሚጠበቅ ይመስለኛል፡፡

የኤክስፖርቱን ዘርፍ የአንድ ሩብ ዓመት ስኬትን ብንመለከት እንኳን ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የወጪ ምርቶቻችን በተላኩበት ሀገር ስንመለከታቸው ወደ 4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ የሚያስገኙ አንድ ነጥብ 25 ሚሊዮን ቶንም ወደ 33 ሀገራት ተልኳል፡፡ ምርቱ ከተላከባቸው ሀገራት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙ አስር ሀገራት በቅደም ተከል ብንመለከት እንኳን፤ ቻይና፣ ጀርመን፣ ሶማሊያ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ኔዘርላንድ፣ ሱዳን፣ ስዊዘርላንድ፣ ዩናይትድስቴትና ጅቡቲ ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህና ከሌሎች ሀገራት የተገኘው ገቢ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ያህል ሆኗል፡፡ ይህ የሚያሳየውም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ በዘርፉ የተያዘው ግብ ስኬታማ እንደሚሆን ነው።

ስራ አጥነትን በመቀነስ ረገድም በገጠርም ይሁን በከተማ ከፍተኛ ውጤት መገኘቱን መገንዘብ ጠቃሚ ይመስለኛል። ለአቅመ-ስራ የደረሰ ማንኛውም ዜጋ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማዕቀፍ ውስጥ ገብቶ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛል። ዜጎችን በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲደራጁ በማድረግና ወደ ተጨባጭ ስራዎች ገብተው ራሳቸውን እንዲችሉ በመደረጉ የስራ አጥነት ደረጃ በደረጃ እየተቀረፈ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን እንደ ባዕዳን ሁሉንም ነገር አይሳካም በማለት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ተቀምጠው ለሚተነብዩት ፀሐፊ ተብዬው ምላሽ ብዙ ማለት የሚቻል ቢሆንም፤ በየጊዜው በመፈጠሩ የኢንዱስትሪ ተቋማት፣ በብድር አቅርቦት እንዲሁም በተለያዩ ማህበራት ዜጎች እንዲደራጁ በማድረግ መንግስት የፈጠረውን የስራ አጥ ቅነሳን አዲስ አበባ ውስጥ እንዲሁም በክልሎች ተዘዋውሮ መመልከቱ ዕውነታውን ከምንጩ ለማወቅ ያግዛል። እናም የአዲስ አድማሱ ሰውዬ ከራሳቸው ተቃርኖአዊ ስሜት በመነሳት ሆን ብለው ሀገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑትን ሃቆች ለማየት ሳይፈልጉ በደፈናው የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር ጠምዝዘው ለማውገዝ መሞከራቸው አሳፋሪ መሆኑን መረዳት ያለባቸው ይመስለኛል– ወረቀትና ብዕር ተገኘ ተብሎ ዕውነታን እየደፈጠጡ የጥላቻ ስሜትን ለማራገብ መሞከር የተፃፈበትን ጋዜጣ ክብር ጭምር ዝቅ የሚያደርግ ነውና። በመሳካት ላይ የሚገኝ ዕቅድን ያለ አንዳች አስረጅ በጭፍን ለማውገዝ መሞከር ሀገራችን እንዳታድግና ህዝቦቿም የድህነት ታሪካቸውን እንዳይፍቁ መመኘት በመሆኑ ከአደናቃፊ አሜኬላ እሾህነት ተለይቶ የሚታይ አለመሆኑንም ማወቅ ያሻል።

እንደ እውነቱ ከሆነ የጨለማው ዘማሪ ፀሐፊ በጥላቻ ስሜት ታፍነው እንዳሉት ኢህአዴግ የአምስት ዓመቱን ዕቅድ በስሜታዊነት ተነሳስቶ አላዘጋጀውም። ምንም እንኳን የዕቅዱ ባለቤት ገዥው ፓርቲ ቢሆንም፤ አብዛኛው የዕቅዱ ክፍል በህዝቡ ከፍተኛ ተነሳሽነት የሚፈፀም መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። መንግስት ለብቻው እንዲፈፅመው ተደርጎ አይደለም የተቀረፀው። እናም የልማት ትልሙ የህዝቡ ነው ማለት ይቻላል። እዝብ ደግሞ አመዛዛኝ እንጂ እንደ ፀሐፊ ተብዬው ስሜታዊ ሊሆን አይችልም–ምንግዜም ትክክልና ሚዛናዊ ፈራጅ ነውና። በመሆኑም ዮሐንስ ሰ. በቀጥታ እየሰደቡት ያለው ህዝቡን መሆኑን የገባቸው አይመስልም። ለነገሩ እንኳንስ በመንግስት ደረጃ ህዝብና ሀገር የሚለወጡበት እንዲሁም ህዳሴያቸውን ለማረጋገጥ የንጣፍ ድንጋይ ሆኖ የሚያገለግል ዕቅድ ቀርቶ፤ በግለሰብ ደረጃ የሚዘጋጅ የቤተሰብ ዕቅድም ቢሆን ከስሜታዊነት የራቀ ነው። እርግጥ ከአቶ ዮሐንስ ሰ. የሚጠበቀው እንዲህ ዓይነቱ ያገጠጠ አሉባልታ በመሆኑ አባባላቸው ብዙም የሚገርም ነገር የለውም። ቀደም ባሉት ጊዜያቶችም እንደ አምሳዮቻቸው የደፈና ተሟጓቾች መንግስትን በአሉባልታ ሲጥላሉት እንደነበር እናውቃቸዋለንና።

ይሁንና ጨለምተኛው ግለሰብ ላነሱት ጉዳይ ምላሽ እንዲሁም እግረ መንገዱን ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ፤ ‘ዕቅዱ እንዲቀረፅ መነሻ የነበረው ነገር ምንድነው?’ የሚል ጥያቄን ማንሳት

ተገቢ ይመስለኛል። ለምን ቢሉ የልማት ትልሙ የተዘጋጀው መንግስት ካስመዘገባቸው የኢኮኖሚ ዕድገት አኳያ እንጂ ከስሜታዊነት እንዳልሆነ የጨለማው ተዋናዮች እንዲገነዘቡት ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ነው። እንደሚታወቀው በመሰረታዊ የኢኮኖሚ አማራጭ አሁን እየተመዘገበ ያለው የ11 በመቶ አማካይ ዕድገት እንዲሁም በከፍተኛ የኢኮኖሚ አማራጭ የ15 በመቶ ዕድገትን ለማስመዝገብ ነው ዕቅዱ የተተለመው። ይህ ደግሞ ዕቅዱ ይፋ በሆነበት በ2002 ዓ.ም መጨረሻ በፊት በነበሩት ሰባት ተከታታይ ዓመታት ሀገራችን ያስመዘገበችውን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገትን መነሻ ያደረገ ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው ሀገራችን በእነዚያ ዓመታት /እስካሁን ድረስም/ ከሰሃራ በታች ካሉት ነዳጅ የሌላቸው ሀገራት ውስጥ ከ10 በመቶ በላይ ዕድገት ያስመዘገበች ብቸኛዋ ሀገር ናት። እንዲያውም ዓለም በወቅቱ በተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ ባሳለፈባቸው ዓመታት፤ የሀገራችን ኢኮኖሚ ይህ ነው የሚባል ተፅዕኖ ሳይደርስበትና ግለቱን ሳያቋርጥ ዕድገት ማስመዝገብ መቻሉን እናስታውሳለን።

በእነዚያ ዓመታት የተገኘው ዕድገት /ዛሬም ድረስ ቢሆን/ ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ነው። የከተማው ዕድገት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሀገራችን 85 በመቶ የሚሆነው ህዝብ በሚኖርበት በገጠሩ አካባቢ የሚገኘው አርሶ አደር በተገኘው ዕድል ተጠቃሚነቱን ይበልጥ አረጋግጧል። ትናንት እጅ ወደ አፍ በሆነ የአስተራረስ ዘዴ የሚያመርተው ምርት ከራሱ የዓመት ፍጆታ የሚያልፍ እንዳልነበረ የሚታወቀው የሀገራችን አርሶ አደር፤ ዛሬ ከራሱ ተርፎ የከተማውን ህዝብ በመጥቀም ላይ ይገኛል። ገበያ-ተኮር የሆኑ ምርቶችን በመንግስት የተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ማምረት በመቻሉም "የሚሊዮኖች ጌታ" መሆን ችሏል። የዚህ ምስጢር ደግሞ በመንግስት የተነደፉት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች ትክክለኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው። ትክክለኛ መሆናቸው ብቻም ሳይሆን፤ በግብርናው መሪነት ወደ ኢንዱስትሪ መር ልማት መሸጋገራችን አይቀሬ መሆኑንም ያመላከቱም ጭምር ናቸው። እርግጥም ፖሊሲዎቹ፣ ስትራቴጂዎቹና ስልቶቹ አብዛኛውን አርሶ አደር ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረጉ እንዲሁም ሞዴል አርሶ አደሮችን ሚሊዮነር እንዲሆኑ ያስቻሉ መሆናቸው በተግባር ተፈትሸው ተረጋግጠዋል። የልማት ዕቅዱ ከመተለሙ በፊት በነበሩት ሰባት ዓመታት ሀገራችን የ11 በመቶ አማካይ ውጤት እንድታስመዘግብ አድርገዋታልና። እናም የዕድገት ዕቅዱ መነሻ ይህ ታላቅ ሀገራዊ ስኬት እንጂ "ስሜት" እንዳልሆነ ሐሰት ደርዳሪው ራሳቸው ከሚያራግቡት የቀርጦ ቀጥል ስሜት ወጥተው መረዳት ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ።

ከዚሁ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰንካላ ትችቶች ሳንወጣ በአዲስ ጉዳይ መፅሔት ላይ ጌታቸው የተባሉ ፀሐፊ "...ዕቅዱ ሊጠናቀቅ ሁለት ዓመት በቀረበት በአሁኑ ወቅት የባቡር መስመር ዝርጋታን በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመቀሌ፣ የወልዲያና የታጁራ መስመሮች የአዋጭነት ጥናት የተጠናቀቀው በቅርቡ ነው ማለታቸው እንዲሁም የሌሎቹንም

ለማጠናቀቅ አስር ወር ይወስዳል ሲሉ መናገራቸው እንዴት ነው ነገሩ አያስብልም እንዴ?" የሚል ጥያቄና ግርምትን አቅርበዋል። እኔ በበለኩሌ በባቡር ስራው ላይ "እንዴት ነው ነገሩ?" የሚያስብል ጉዳይ የለም ባይ ነኝ። አዎ! ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው እንደገለፁት በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ላይ የተቀመጠው የባቡር መስመር ዝርጋታ ያለ አንዳች የገንዘብ ችግር በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተከናወነ ነው። እርግጥ የባቡር ግንባታ ስራ ባድ ነው። ሌላው ቀርቶ ጥናት ለማድረግና የሰው ሃይልን ለማብቃት የሚወስደው ጊዜ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ሀገራችን ለባቡር ግንባታ ስራዎች ገና አዲስ በመሆኗም በመስኩ የሰለጠነ የሰው ሃይል ያስፈልጋታል። እናም በዚህ ረገድ መንግስት ከሀገሪቱ የቴክኖሎጂ ተቋማት ጋር በመነጋገር በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይልን በማፍራት ላይ ይገኛል። ምናልባትም በስራው ላይ የሚታይ መጓተት ካለ በአፈፃፀም ዙሪያ ሊኖሩ ከሚችሉ ተግዳሮቶች አንፃር ሊሆን ይችላል። ይህን ደግሞ እንደማንኛውም የማስፈፀም ተግባራት ሁሉ በመንግስት መፍትሔ እየተሰጠው ሊስተካከል የሚችል ጉዳይ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የባቡር ስራው አለመስተጓጎሉን መገንዘብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በጥቅሉም ሁሉም የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቀዶች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆኑን ከአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ሃቁን መረዳት ቢያንስ በደፈናውና ዕውነት ላይ ባልተበሰረተ መንገድ ከመፃፍ የሚያድን ይመስለኛል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህን በተመለከተ ለፓርላማ ያቀረቡት ሪፖርትም መታየት ያለበት ከዚህ ነባራዊ ሃቅ አኳያ መሆን ይገባዋል።

አቶ ሃይለማርያም ለፓርላማው ከሰጡት ማብራሪያዎች ውስጥ ተነጥሎ ተወስዶ የተብጠለጠለው ሌላኛው ጉዳይ ስለ ሂዮማን ራይትስ ዎች የተነሳው ነጥብ ነው። የአዲስ ጉዳይ መፅሔቱ "ሐሳብ አለኝ" አምድ ፀሐፊው አቶ ጌታቸው "...ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሂዮማን ራይትስ ዎች ያወጣውን ሪፖርት አስመልክቶ ትክክል አይደለም፣ ተሳስቷል ማለት ሲችሉ መንግስት ከዚህ ቀደም ያደርገው የነበረውንና ትችት የሚሰነዝርበትን የማጥላላት ዘመቻ በመድገም 'ከሂዮማን ራይትስ ዎች ጋር ያለን ልዩነት የርዕዮተ-ዓለም ነው' ማለታቸው 'እኚህ ጠቅላይ ሚኒስትር ምን ነካቸው?'" ሲሉ አግራሞት መሰል አደናጋሪ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩት መሬት ላይ ያለውን አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም የሆነውን የሂዮማን ራይትስ ዎችን ትክክለኛ ማንነት ነው። እርግጥም አንዳች ነገር የነካቸው አክራሪውን ተቋም ለመከላከልና የኢትዮጵያን አቋም በባንዳነት ተሰልፈው "የማጥላላት ዘመቻ" ያሉት አጨብጫቢው ግለሰብ ናቸው። ፀሐፊው በዚህ አባባላቸው እጅግ በሚያሳፍር ሁኔታ ፈረንጅ አምላኪ በመሆን ሁለት ስህተቶችን ፈፅመዋል። የመጀመሪያው ሂዩማን ራትስ ዎች ገመናው እንዳይታወቅ ለመሸሸግ መሞከራቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በዕውቀት አጠርነት የማያውቁትን ነገር ለማውራት መከጀላቸው ነው።

ዳሩ ግን እርሳቸው ምንም ይበሉ ምን፤ አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም ከሀገራችን ጋር የገጠመው የርዕዮተ-ዓለም ጦርነት ይህን ይመስላል።…በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በምዕራቡና በምስራቁ ሀገራት መካከል የተፈጠረውን የርዕዮተ-ዓለም የበላይነትን ለመቀዳጀት ሄልሲንኪ ላይ "ሄልሲንኪ ዎች" በሚል ስያሜ በምዕራብያኑ እንዲቋቋም የተደረገው ይህ ተቋም፤ በቁም ትርጉሜው "ሂዩማን ራይትስ ዎች" የሚለው መጠሪያ "የሰብዓዊ መብት ጥበቃን" የሚያመላክት ቢሆንም፤ ላዩ ላይ ከለጠፈውከዚህ ስያሜ ጋር ግን አይተዋወቅም፡፡ ከዚህ ይልቅ 'በመጠሪያው ማንነት ጭንብል ተጀቡኖ ድብቅ ፖለቲካዊ አጅንዳን የሚያራምድ ፅንፈኛ ድርጅት ነው' የሚለው እሱነቱ ይበልጥ ይስማማዋል፡፡ ክቡሩን የሰው ልጅ መብት በታዛነት ተጠልሎ የራሱን ርዕዩተ - ዓለማዊ አስተሳሰብ ነባራዊ ሁኔታቸውን ተመርኩዘው የተለየ የልማት አማራጭን በሚከተሉ ሀገሮች ላይ በኃይል ለመጫን የሚጥረው ይህ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ድርጅት፤ የገንዘብ ምንጬ ጆርጅ ሶሮስ የተባለ አክራሪ የኒዮ - ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ የፈጠረው ከበርቴ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

እናም እኒ ሚስተር ሶሮስ ዋነኛ ዓላማቸው ባለረብጣ ዶላር ያደረጋቸውን የኒዮ - ሊበራሊዝም ርዕዮተ - ዓለም ልዕልና እንዳይከስምና ማንኛውም ሀገር በዚህ አስተሳሰብ ብቻ እንዲመራ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ በመሆኑም ሂዩማን ራይትስ ዎች የእነዚህንና መሰል አክራሪ ተቋማትን መልዕክት ተቀብሎ ገቢራዊ ለማድረግ ይጥራል።ተልዕኮውም በራሳቸው የልማት አቅጣጫ ማደግ በመጀመሩ ሀገራት ውስጥ የእነ ሚስተር ሶሮስና መሰሎቻቸው ህልም የሆነውን የቀለም አብዮት በማስነሳት፤ ከቻለ የመንግስት ለውጥ ማድረግ፤ ይህ አልሳካም ካለው ደግሞ የመንግስታቱን መልካም ስም እንደ "አቡነ ዘ-በሰማያት" እየደጋገመ በሚያወጣው የሪፖርት ጋጋታ ማጠልሸት ነው፡፡ ሀገራችን ደግሞ ራሴ የቀየስኩት ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንጂ ኒዮ-ሊበራሊዝም አያዋጣኝም በማለት የሯሷን የኢኮኖሞ ዕድገት ተከትላ በማገድ ላይየምትገኝ ናት። እናም የአክራሪ ቡድኑ የውሸት ሪፖርት ሰለባ ልትሆን ችላለች። እንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው ከዚህ ቡድን ጋር ያለን ግንኙነት የርዕዩተ-ዓለም ነው ያሉት ከዚህ ነባራዊ ዕውነታ በመነሳት መሆኑን እውቀት አጠሩ ፀሐፊ ሊገነዘቡት ይገባል።

እርግጥ ፅንፈኛው የእነ ሚስተር ሶሮስና አምሳያዎቻቸው ተላላኪ ድርጅት ሀገራችን ውስጥ ይህ ነው የሚባል በይፋ የተደራጀ መዋቅር የለውም። ብቸኛ የወሬ ቋቶቹ በንድፈ -ሃሳብ ደረጃ 'ህገ - መንግስቱን አክብረን እንንቀሳቀሳለን' የሚሉ፤ ነገር ግን በተግባር ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ህገ-መንግስቱን ቀዳድደው ከመጣል ወደ ኋላ የማይሉ ተቃዋሚ ተብዬዎች፣ እንደ ፀሐፊው ዓይነት አጨብጫቢዎችና ሀገራችን በህዝብ ጨራሽ ምግባራቸው በአሸባሪነት የፈረጀቻቸው ቡድኖች ናቸው፡፡ የእነዚህ ኃይሎች ምስክርነት ደግሞ ምን ሊሆን እንደሚችል ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሃይሎች ለህዝብ ካላቸው የጠላትነት ስሜት በመነሳት

ያልተፈጠረን ነገር እንደተፈጠረ፣የተከናወነን ነገር እንዳልተከናወነ በመቀላመድ  በቅዥት ዓለም ውስጥ የሚዳክሩ  ለጥፋት የተሰለፉ  በመሆናቸው  ነው፡፡ እናም ከፅሑፋቸው በመነሳት ምናልባትም ፀሐፊው የእነዚህ ወገኖች ባልደረባ አሊያም ነፀብራቅ ሳይሆኑ የሚቀሩ አይመስለኝም– ከመሬት ተነስተው ዓለም በፖለቲከኝነቱ የሚያውቀውን አክራሪ ቡድንን ማንነት ሊሸሽጉ እንዲሁም ዋስና ጠበቃው ሆነው በጭፍን ሊከራከሩ አይችሉምና።

አቶ ኃይለማርያም ቱሎው ኦይል የተሰኘው ኩባንያ በኢትዮጵያ ነዳጅ ሊገኝ የሚችልበትን ፍንጭ መናገሩን ተከትሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ “ማደናገሪያ ነው፣ የውጭ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ያለው ነው” ማለታቸውንም በሚያስገርም ሁኔታ አግባብነት እንደሌለው ቆጥረውታል–እኚሁ አዲስ አበባ ቁጭ ብለው ሃሳብ አለኝ የሚሉት ፅንፈኛ ፀሐፊ። በመጀመሪያ ደረጃ ግለሰቡ ስለ ነዳጅ ፈላጊ ኩባንያዎች ያላቸው ግንዛቤ ምንም ሊባል የሚችል ነው። ስራው በመንግስታት ደረጃ የሚከናወን ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ማዕድን ፈላጊ ኩባንያዎች ከፍተኛ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። እናም አብዛኛዎቹ የከርሰ-ምድር ማዕድን ፈላጊዎች ብዙን ጊዜ ስራቸውን እያቋረጡ የሚሄዱት ስራው በውስብስብነቱ ከሚወስደው ረጅም ጊዜ አንፃር የገንዘብ እጦት ስለሚያጋጥማቸው መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ይህን ችግራቸውን ለመቅረፍ የሚጠቀሙበት ዘዴ ለአበዳሪዎች አላስፈላጊ ተስፋዎችን በመስጠት ከተለያዩ ባንኮች ገንዘብ የሚያገኙበትን አማራጮችን በመፈለግ ነው። ምንም እንኳን ይህ ተግባራቸው ነዳጅ እናገኝለታለን ካሉት ህዝብ አኳያ አግባብነት የሌለው ቢሆንም፤ ኩባንያዎቹ ግን የእንጀራ ጉዳይ ነውና ይህን መሰሉን ማደናገሪያ ከመጠቀም ወደ ኋላ አይሉም። በመሆኑም የቱሎው ኦይል ኩባንያ ያልተጨበጠ ተስፋና የተሳሳተ መረጃ መታየት ያለበት ከዚህ አኳያ ይመስለኛል።

እርግጥ ሀገራችን ውስጥ ነዳጅ ቢገኝ የሚጠላ ሰው ያለ አይመስለኝም። በሀገራችን ዘርፉ እንደ ዋነኛ የኢኮኖሚ ምንጭ የሚታይ ባይሆንም፤ የልማት ዕቅዶችን በመደገፍ ረገድ የበኩሉን ድርሻ ሊያበረክት ይችላል። ይሁንና የኩባንያው የተሳሳተ መግለጫ መታየት ያለበት ገና ባልተረጋገጠ ጉዳይ ላይ አላስፈላጊ ተስፋን በህዝቡ ውስጥ የሚያጭር ሊሆን ስለሚችል እንደሆነ ሁሉንም ነገር የመቃወም አባዜ የተጠናወታቸው ፀሐፊ ማወቅ ይኖርባቸዋል። እርግጥ የተባለው ነዳጅ ተገኝቶ ቢሆንና ለህዝብ ቢነገር ምንም ክፋት የለውም። ግና ኩባንያው ፋይናንስን ከአበዳሪዎች ለማግኘት ሲል በህዝብ ስሜት ለመጫወት መሞከሩ አግባብነት ያለው አይመስለኝም። ማንኛውም ህዝብ እንደ ህዝብ መከበር አለበትና።

ሌላኛው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ ዙሪያ የተነሳውና አንድ ተንጠልጣይ ወሬን ካገኘ የራሱን ግብረ-አበሮች ከያሉበት በባትሪ ፈልጎ “በተንታኝ” ስም በመጥራትና የኢትዮጵያን መንግስት እንዲያጥላሉ በማድረግ የሚታወቀው የአሜሪካው ድምፅ የአማርኛው አገልግሎት ያነሳው

የሰራዊታችንን የሶማሊያ ቆይታን የተመለከተ ጉዳይ ነው። እርግጥ አቶ ኃይለማርያም ለፓርላማ አባላት ለቀረባቸው ጥያቄ ሰራዊታችንን ከሶማሊያ ለማስወጣት ፍጥነት ያለው ስራ እንደሚከናወን ተናግረዋል። አክለውም አሁን ባለው ሁኔታ ሰራዊቱን ከሶማሊያ እንደማያስወጡ አስታውቀዋል። ከእርሳቸው የፓርላማ ውሎ በኋላም ቢሆን ኒውዮርክ የተጓዙትና ስለ አፍሪካ ግጭት አወጋገድ ለፀጥታው ምክር ቤት ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ቴዎድሮስ አድሃኖምም "ኢትዮጵያ ሰራዊቷን ከሶማሊያ በማስወጣት ኃላፊነቷን አታሳንስም" በማለት አስረድተዋል። ግና የዋሽንግተኖቹ የአማርኛው ክፍል ጋዜጠኛ መሳይ ፖለቲከኞች ግን በውስጣቸው የሚጋጭ ነገር አገኘን በማለት የሁለቱን ባለስልጣናት ንግግር ለማራገብ ሞክረዋል።

ዳሩ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰራዊታችንን ከሶማሊያ ለማስወጣት ፍጥነት ያለው ስራ መከናወን እንዳለበት እንዲሁም አሁን ባለው ሁኔታ ሰራዊቱ እንደሚቆይ የተናገሩትና አቶ ቴዎድሮስ ለፀጥታው ምክር ቤት ሀገራችን ያለባትብ ቀጣናዊ ሃላፊነት አውስተው ሰራዊታችን ከሶማሊያ እንደማይወጣ ያስረዱበት አካሄድ አንድና አንድ ነው። የቃላት ልዮነት ካልሆነ በስተቀር ፍሬ ጉዳዩ አይለያይም። የዋሽንግተኖቹ የቀድሞው ስርዓት ናፋቂዎች፣ የኢህአፓ ርዝራዦችና አመፅ ተንታኝ ጋዜጠኞች እንዳሰቡት ምንም ዓይነት ልዮነት የለውም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰራዊታችንን ከሶማሊያ ለማስወጣት ፍጥነት ያለውን ስራ እናከናውናለን ሲሉ፤ ከሶማሊያ መንግስት በተጨማሪ ከሌሎች ሰላም አስከባሪዎች ጋር በተጠናከረ ሁኔታ በመስራት የምስራቅ አፍሪካው የአል-ቃዒዳ ክንፍ የሆነውን አል-ሸባብን ከዚያች ሀገር ልሳነ-ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠራርገን እናስወጣዋለን ማለታቸው ነው። ይህ ተግባር የሚከናወነው ሰራዊታችን ከሶማሊያ ሳይወጣ የሚፈፀም መሆኑን ለማመላከትም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ሰራዊቱ እዚያው እንደሚቆይ በአደባባይ ገልፀዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም ቢሆኑ በኒውዮርክ ንግግራቸው ይህንኑ ነው የደገሙት–የከባቢው ሀገራት ጠንቅ የሆነው አሸባሪው አል-ሸባብ እስካልተወገደ ድረስ ሰራዊታችን ወንድም የሆነውን የሶማሊያ ህዝብ በመከላከል ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንደሚወጣ በማስረዳት። እናም በእኔ እምነት የሁለቱ ባለስልጣናት ንግግር ለቪ.ኦ.ኤዎቹ ሰዎች የተለያየው በእነርሱ የተበረዘ ጭንቅላት ውስጥ ብቻ ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን እኔ እስከሚገባኝ ድረስና ነገሩን በውል ለመረዳት ሰራዊታችን ሶማሊያ ውስጥ የሚገኘው በሁለት ምክንያቶች መሆኑን መገንዘብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። አንዱ ሀገራችን በአፍሪካም ይሁን በቀጣናው ውስጥ ያላት ታሪካዊ ኃላፊነት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ እመርታ ከሚኖረው ፋይዳ አኳያ ተመዝኖ ነው። አዎ! ሀገራችን የአፍሪካ ህብረት መስራችና የአህጉሪቱ መዲና እንደመሆኗ መጠን አፍሪካዊ ኃላፊነቶችን በግንባር ቀደምትነት መውሰድ ይኖርባታል፤እንዲያውም የውዴታ ግዴታዋ ጭምር ይመስለኛል። በዚህም ምክንያት ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብ የአሸባሪዎችና

የፅንፈኞች መፈንጫ ሲሆንና ለዓመታት ሰላሙን አጥቶ በየስደተኛ ማቆያ ስፍራዎች ሲንገላታ ማየት ኢትዮጵያን ከመሰለ የአፍሪካ አውራ ሀገር ዝም ማለት የሚጠበቅ አይመስለኝም። እናም በአፍሪካ ህብረት ውስጥ ካላት ቁልፈ ሚና በተጨማሪ፤ በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግስት ለሀገራችን ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ሰራዊቷን አሰማርታለች—ለህዝብ ካላት ልዩ አክብሮት በመነጨም ጭምር።

ከዚህ ባሻገርም በጎረቤት ሶማሊያ ውስጥ የሚኖር ሰላምም ይሁን ቀውስ ሀገራችን ተጠቃሚ አሊያም ተጎጂ መሆኗ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። በመሆኑም አሸባሪው አል-ሸባብ በሀገሪቱ መመስረት የሚፈልገው የአክራሪዎች ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በመሆኑ በሀገራችን ላይ በግልፅ ሊታይ የሚችል አደጋን ደቅኗል። እንዲያውም ኢትዮጵያን በጠላትነት በመፈረጅ ሀገራችን ላይ የጅሃድ ጦርነት አውጆብናል። ይህም በብሔራዊ ጥቅማችን ላይ የተጋረጠ ከባድ አደጋ ነው። እናም ይህን ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል ማዳከም ብሎም ማጥፋት የግድ ነው። ለዚህም ነው መከላከያ ሰራዊታችን ከሞቃዲሾ መንግስትና ከአፍሪካ ህብረት ሰላም አስከባሪዎች ጋር በመቀናጀት አል-ሸባብን አዳክሞ ትርጉም በሌለው ደረጃ እንዲንቀሳቀስ እና እንዲጠፋ ለማድረግ በቅርበት እየሰራ የሚገኘው። ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በአንድ ቋንቋ እንዳሉት ሰራዊታችን የተሰጠውን አፍሪካዊ፣ ቀጣናዊና ሀገራዊ ብሎም ህዝባዊ ተልዕኮውን ሳይፈፅም ወደ ሀገሩ የማይመለሰው። አማን ያሰንብተን።